# የልጅን መረጃ ማጋራት
# Child Information Sharing

Amharic | አማርኛ

## ለምን መረጃዬን ለማጋራት ፈለጋችሁ?

### የቪክቶሪያ ልጆችን መንከባከብ

ሁሉም የቪክቶሪያ ልጆች ደህንነቱ የተጠበቀ እና ደስተኛ ህይወት እንዲኖሩ ለመርዳት፣ የቪክቶሪያ መንግስት ከልጆች ጋር የሚሰሩ የተወሰኑ ባለሙያዎች መረጃ የሚለዋወጡበትን መንገድ እያሻሻለ ነው።

ብዙ አገልግሎቶች አስቀድመው መረጃን ይጋራሉ። የልጅን መረጃ መጋራት መርሃ ግብር (Child Information Sharing Scheme [CISS]) እነዚህ ባለሙያዎች ምን ዓይነት መረጃ ማጋራት እንደሚችሉ እንዲረዱ፣ የቤተሰብን ግላዊነት እንዴት እንደሚጠብቁ እና አብሮአቸው የሚሰራውን (የሚረዱትን) ልጅ ሙሉ ስዕል ማየት እንዲችሉ ቀላል ያደርግላቸዋል።

በሕይወታቸው በአንድ ወቅት፣ ብዙ ልጆች በተወሰነ ደረጃ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል። ከተወለዱበት ጊዜ ጀምሮ፣ 18 ዓመት እስኪሞላቸው ድረስ፣ የሕጻናት መረጃ መጋራት ማሻሻያ ልጆች እና ቤተሰቦቻቸው ከባለሙያዎች እና ድርጅቶች የተሻለ ድጋፍ እንዲያገኙ ይረዳቸዋል።

## ቤተሰቦችን የሚረዳው እንዴት ነው?

## ባለሙያዎችን የሚረዳው እንዴት ነው?

የልጅን መረጃ መጋራት፣ ልጆችን የሚደግፉ እና የሚንከባከቡ ባለሙያዎች (እንደ አስተማሪዎች እና ነርሶች ያሉ) ስለ አንድ ልጅ ያላቸው እውቀት እርስ በርሳቸው ማለትም አንዱ ለሌላው እንዲጋሩ፣ ብሎም ለሌላው ምን ዓይነት መረጃ እንደሚያጋሩ እና እንዴት የቤተሰብን ግላዊነት መጠበቅ እንደሚችሉ ላይ መመሪያዎችን እንዲሰጡ ያስችላቸዋል።

## ለምሳሌ፡-



ታጅ ትምህርት ቤቶችን ቀይሯል። አዲሷ መምህሩ ሳራ በክፍል ውስጥ ለመናገር እንደማይፈልግ እና የትምህርት ቤት ስራውን ለመጨረስ እንደሚቸገር አስተውላለች። ከታጅ የቀድሞ ትምህርት ቤት መረጃ በመጠየቅ፣ ሳራ ዲስሌክሲያ እንዳለበት ተረድታለች፣ ይህ ነው በክፍል ውስጥ ለመሳተፍ እንዲያመነታ ያደረገው።

**ይህ የታጅ አስተማሪ የታጅ የመማር ፍላጎትን የሚደግፍ የትምህርት እቅድ እንድትፈጥር ስለሚያስችላት፣ በልጅ መረጃ ማጋራት በኩል ለሌሎች ሊጋራ የሚችል የመረጃ ምሳሌ ነው።**

# ከማን ጋር ነው የምትጋራው? እንዴትስ ጥቅም ላይ ይውላል?

## የተጋራው የመረጃ አይነት

የልጆችን ደህንነት ወይም ህልውና የሚደግፍ ማንኛውም መረጃ ሊጋራ ይችላል። ይህ ህፃኑ የሚቀበለው እንደ ሙያዊ ድጋፍ ያለ መረጃ ሊሆን ይችላል፣ ወይም ስለ ቤተሰብ ግንኙነቶች ግንዛቤ ሊሆን ይችላል።

## መረጃው ለምን ጥቅም ይውላል

ታሪክህን ሁለት ጊዜ መናገር እንዳይኖርብህ ያረጋግጣል

ሊረዱ የሚችሉ ትክክለኛ ሰዎችን ማሳተፍ

ሙሉ ምስሉን ማየት

ልጆች እንዲያድጉ መርዳት

## መረጃውን ሊያይ እና ሊያጋራ የሚችለው ማን ነው?

መረጃን የማካፈል ስልጣን ያላቸው የተወሰኑ ሰዎች ብቻ ናቸው - ሁሉም አይደሉም። እነዚህ ሰዎች እንደ መምህራን፣ ዶክተሮች፣ ማህበራዊ ሰራተኞች እና አማካሪዎች፣ ነርሶች እና ፖሊስ ያሉ ልጆችን የመንከባከብ እና የመጠበቅ ግዴታ ያለባቸው ባለሙያዎች ናቸው።

## ለምሳሌ፦



ሊዛ ከአሊስ ጋር እና የአምስት ዓመቷ ሴት ልጇ ጃስሚን፣ ትንሽ የልብ ህመም ያላት ልጇ ጋር ትሰራ የነበረች የትምህርት ቤት ነርስ ነች። ጃስሚን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርቷን ስትጀምር ሊሳ ከአሊስ ጋር ትናገራለች እና ስለ ጃስሚን ሁኔታ መረጃን ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነርስ ጋር ለመጋራት ያላትን አመለካከት ለማወቅ ትፈልጋለች ይህም ፍላጎትዋን እንዲያውቁ ለማድረግ ነው። ሊዛ መረጃውን ለሌሎች ከማካፈሏ በፊት የአሊስን አመለካከት ታውቃለች።

**ይህ አንድ ባለሙያ መረጃን ለማጋራት እንዴት እንደሚመርጡ እና ከማን ጋር ማጋራት እንደሚችሉ የሚያሳይ ምሳሌ ነው።**

# መቼ ነው መረጃ ማጋራት የሚቻለው?

## ለሚከተሉ ጉዳዮች ካልሆነ በስተቀር መረጃ ማጋራት አይቻልም፡-

1. **የልጁን (ወይም የልጆችን) ደህንነት ወይም ህልውና ለማስተዋወቅ ጥቅም ላይ የሚውል ከሆነ።**
2. **መረጃ ማጋራት አገልግሎቶችን ለመስጠት፣ እቅድ ለማውጣት ወይም በልጆች ላይ የሚደርሱ አደጋዎችን ለመመርመር ወይም ለመቆጣጠር የሚረዳ ከሆነ።**
3. **ማንንም አደጋ ላይ የማይጥል ከሆነ፣ በህጋዊ መንገድ የተከለከለ ከሆነ ወይም በመመሪያው ውስጥ ካልተካተተ።**

መረጃ ከመጋራቱ በፊት መሟላት ያለባቸውን ሁኔታዎች ሙሉ ዝርዝር ለማግኘት፣ www.infosharing.vic.gov.auን ይጎብኙ።

## መረጃ እንዴት ይጋራል?

በህጋዊ መንገድ የተፈቀደላቸው ድርጅቶች እና ባለሙያዎች መረጃን መጠየቅ ወይም ለማጋራት መወሰን ይችላሉ።

## መረጃን ሚስጥራዊ እና ደህንነቱ የተጠበቀ ማድረግ

ልጆችን የመጠበቅ አንዱ አካል መረጃቸው ደህንነቱ የተጠበቀ እና በደህና መቀመጡን ማረጋገጥ ነው። የልጅ መረጃ ማጋራት መረጃ መቼ ማጋራት እንደሚችሉ ባለሙያዎችን በመንገር ነባር የግላዊነት ህጎችን ይደግፋል። ሚስጥራዊ መረጃን በማይፈለግበት ጊዜ ማካፈል ወንጀል ነው። በተጨማሪም፣ ሁሉም መረጃዎች ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ በያንዳንዱ ድርጅት መቀመጥ አለባቸው። ለሚመለከታቸው ሰራተኞች ስልጠና ተሰጥቷል፣ ስለዚህ ሃላፊነታቸውን ያውቃሉ።

## ለምሳሌ፡-

አንዲ የማሕበራዊ ድጋፍ ሰራተኛ ነው፣ እናም ከአንድ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተማሪዎች ምዝገባ መኮንን ስለ ሊ መረጃ እንዲያጋራ ጥያቄ ቀርቦለታል። አንዲ ለአጭር ጊዜ ቤት አልባ በነበሩበት ጊዜ የሊን ቤተሰብ ደግፏል። ከሊ እና ከቤተሰቡ ጋር ከተማከረ በኋላ፣ አንዲ ስለ ኑሮ ሁኔታቸው መረጃን ማጋራት አልፈለገም፣ ምክንያቱም ይህ መረጃ ሊ በትምህርት ቤት እንዳይመዘገብ ሊጠቀሙበት ይችላሉ የሚል ጥርጣሬ አለው።

**ይህ ባለሙያዎች መረጃን ማጋራት የማይችሉበት ምሳሌ ነው - የተማሪዎች ምዝገባ (መግቢያ) መኮንን ስልጣን ያለው ባለሙያ አይደለም፣ እና መረጃው የሊ ወይም የቤተሰቡን ደህንነት ወይም ህልውና ለመደገፍ ጥቅም ላይ አይውልም።**

# ቅሬታዎች (ስሞታዎች)

## መረጃው ባልተፈቀደ መንገድ ተጋርቶ ሊሆን ይችላል የሚል ስጋት ካለዎት አስተያየት የመስጠት እና ቅሬታ የማቅረብ መብት አለዎት።

ቅሬታ ካለዎት በመጀመሪያ ደረጃ መረጃውን ካካፈልዎት ድርጅት ጋር ይነጋገሩ። ሁሉም ድርጅቶች ቅሬታ የሚሰሙበት ስርዓት እና ደንብ ሊኖራቸው ይገባል።



## ጉዳዩ እንደተፈታ ካልረኩ፣ ቅሬታ ለሚከተለው ሊቀርብ ይችላል፦

**ቅሬታው ስለግል መረጃ ከሆነ የቪክቶሪያ መረጃ ኮሚሽነር ቢሮን ያነጋግሩ**

ድረ ገጽ፦ ovic.vic.gov.au / ስልክ ቁጥር፦ 1300 666 444

**ቅሬታው የጤና መረጃን በሚመለከት ከሆነ የጤና ቅሬታዎች ኮሚሽነርን ያነጋግሩ**

ድረ ገጽ፦ hcc.vic.gov.au / ስልክ ቁጥር፦ 1300 582 113

## ስለ ልጅ መረጃ መጋራት መርሃ ግብር ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ የሚከተሉትን ማድረግ ይችላሉ፦

**ይደውሉልን፦** 1800 549 646

**ይጻፉልን፦** CISandFVIS@education.vic.gov.au

**ድረ ገጻችን ይጎብኙ፦** vic.gov.au/child-information-sharing-scheme

CHILD INFORMATION SHARING SCHEME

VICTORIA State Government